የአገልጋይነት ሥርዓት

ሱዌህ ዩ ክዎንግ
(Hsueh Yu Kwong)

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የፖ.ሣ. ቁጥር 127፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የአገልጋይነት ሥርዓት

The Discipline of Servanthood
by Rev. Hsueh Yu Kwong
First Printing August 2013

Published by: SINGAPORE EVERY HOME CRUSADE CO. LTD
No.8 Guilin Building, #02-04, Lorong 27A Geylang,
Singapore 388106

In Association with
SIM EAST ASIA LTD
116 Lavender Street, #04-09 Pek Chuan Building,
Singapore 338730

This book is translated and published by
SIM Publication, Box 127, Addis Ababa, Ethiopia
with the kind permission of Mrs. Lily Hsueh
(Rev. Lily Ho Swee Hoo) -NB፡ email of Feb. 9, 2015.
Email: simethiopia.publication@gmail.com
ይህ መጽሐፍ በኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ የተተረጐመውና የታተመው
በሚስስ ሊሊ ሆስዌሁ መልካም ፈቃድ ነው
(የፌብርዋሪ 9 ቀን 2015 ኢ-ሜይል ይመልከቱ)።

ትርጉም፡- ፈቃዱ ገብሬ
እርማት፡- ኃይሉ ልመንህ
ዋና አርታዒ ፡- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ አቀማመጥ፡- ጥሩወርቅ በቀለ
የመጀመሪያ እትም 2009 ዓ.ም
First printing 2016

ማውጫ

I. መቅድም 5

II. የአርታዒው ማስታወሻ 13

III. መግቢያ 14

ክፍል 1

የአእምሮ ሥርዓት

1. እነሆኝ 18
2. የልብህን ዝንባሌዎች አሠልጥን 22
3. የመንታ ልብ አደጋዎች 26
4. ጥሪ እና ተግዳሮት 29
5. በቅድስና ጉዞ ላይ 34
6. የራስ መሰጠት በተግባር የሚታይ ነው 41
7. ራስን የመሰጠት ትክክለኛው ትርጉም 43
8. እጅግ ውድ የሆነውን ነገር ስጡ 48
9. በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የማይጠቅም አገልጋይ ማን ነው? 55

ክፍል 2

የአገልጋይ ምሳሌነት

10. የኢየሱስን ዱካ መከተል 60
11. ተምሳሌት፡- መጥምቁ ዮሐንስ 64
12. በዛሬው ዓውድ ውስጥ የሚያገለግል 71
13. ለእግዚአብሔር መንግሥት መልካም ወታደሮችን ማሠልጠን 76
14. በእምነት መምራት 85
15. በፍቅር ማድረግ 95
16. ንግግራችሁ የሚያንጽ ይሁን 104
17. በሕይወት ምስክር ሁኑ 113
18. የመከራን ጽዋ ለመጠጣት ፈቃደኛ ሁኑ 123
19. በድኽነት ውስጥ የተትረፈረፈ ሀብት 129

20. መከራን ማራቅ የለባችሁም 132
21. በሥቃይና በመከራ ውስጥ ደስታ 137

ክፍል 3

ለአገልግሎት ቃል የገባ

22. ለእግዚአብሔር ምሪት መታዘዝ 141
23. የደስታ ምክንያቶች 152
24. መንፈሳዊ እድገት ወሳኝ ነው 158
25. የመሥዋዕትነት መንገድ 164
26. አገልግሎትን መማር የዕድሜ ልክ ሂደት ነው 176
27. ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ማገልገል 178
28. በአገልግሎታችሁ ሙሉ ሁኑ 182
29. የጽድቅ እና የታማኝነት ሕይወት መኖር 186
30. የወንጌልን ኃይል ማወቅ 191

ክፍል 4

የእድገት ሥርዓት

31. የሐዋርያው ዮሐንስ የመማር ጉዞ 196
32. በእግዚአብሔር ልዩ የማሠልጠኛ ክፍል ውስጥ 202
33. የምትከታተሉት ምንድን ነው? 207
34. አምስት ቀላል የመማር አቋሞች 212
35. የክብር ዕቃዎች ስለ መሆን 220
36. የለእግዚአብሔርን ቃል የሚያዳምጡ ጆሮዎች 226
37. በውጭ አገር መማር ወሳኝ አይደለም 229
38. በእምነት መኖርን ስለ ማካፈል 232
39. የመልካም ባሕርይ ባለቤት መሆንን መማር 235
40. የሥነ መለኮት ተማሪ ወይስ የእግዚአብሔር ተማሪ? 238
41. ቃሉን የማይፈጽም፣ ሰባኪ አይደለም 240

መቅድም

ቢሾፕ (ዶ/ር) ህዋ ዩንግ
የማሌዥያ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን
ሐምሌ 2012 (እ.ኤ.አ)

አዘውትሬ የምካፈልበት የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን በዚያን ጊዜ በፔናንግ፣ አምልኮ ይካሄድበት በነበረው በማድራስ ጎዳና የካንቶኔስ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ነበር። ያን ጊዜ ዕድሜዬ 8 ወይም 9 ዓመት ብቻ ነበር። ይሁንና የተከበሩ ስዌህ ዩ ክዎንግ፣ ከሌሎች ጋር በመሆን፣ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል ሲመጡ አስታውሳለሁ። ከስብከቶቻቸው የትኛውንም አስታውሳለሁ ብዬ በድፍረት ለመናገር አልሞክርም። ነገር ግን ጎብስቱንና ወይኑን ከሌሎች ጋር አብረው ለምእመናን ለማቅረብ ሲዘጋጁ በጌታ ራት ገበታ አጠገብ ተንበርክከው ሳሉ ይታይባቸው የነበረው ፈሪሀ እግዚአብሔርና የትሕትና መንፈሳዊ ባሕርይ አስታውሳለሁ። ስለ እርሳቸው ልረሳው የማልችለው አንድ ልቤን የነካኝ ነገር አለ። ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሕይወታቸውን ስመለከት፣ ለእኔ ለአንድ ለ8 ወይም ለ9 ዓመት ልጅ ትዝታው እንዲህ እንዳይረሳ ያደረገው፣ የእኚህ ታላቅ ሰው ጥልቅ መንፈሳዊነታቸው ነገር ሳይሆን አይቀርም!

ይህ ታዲያ የአገልግሎት ሥርዓት (The Discipline of Servanthood) ወደሚለው የእንግሊዝኛ ትርጉም መጽሐፋቸው ጎትመት ይመራኛል። በዚያን ጊዜ ሰባኪው ፊት ሆኖ ይታይ የነበረውን ትንሽ ልጅ ልብ የነካው ነገር አሁን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተራውን ጠብቆ ምዕራፍ በምዕራፍ እየተገለጠ ነው! እነዚህን ምዕራፎችና ቀደም ሲል ለጎትመት የበቃውን ራሳቸው የጻፉትን የሕይወት ታሪክ መጽሐፋቸውን ገለጥ ገለጥ ሳደርግ፣ የተከበሩ ስዌህ ይታይባቸው የነበረው ያ የትሕትና መንፈሳዊ ባሕርያቸው በምን ምክንያት

በልቤ ይህን ያህል ትዝታ እንደ ቀረጸ በኋላ ላይ መረዳት ጀመርሁ።።

ምናልባት ስለዚህ መጽሐፍ እጅግ ተፈላጊው ነገር፣ 'አገልጋይነት!' የሚለው ማዕከላዊ ርእሰ ጉዳይ ሊሆን ይችላል! ዛሬ ክርስቲያኖች ስለ 'መሪነት' መናገርን ቢመርጡም፣ ነገር ግን ብዙዎች ስለ 'አገልጋይነት' መናገርን አይወዱም። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሪነት የሚያበረታታ አልፎ አልፎ ቢሆንም፣ በአንጻሩ ግን አገልጋይነትን እንድንቀበል ይቀሰቅሰናል።። ይህ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለሥልጣን ቦታ ሲራኮቱ፣ *‹‹በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና››* (ማር. ፲፡44፣45) በማለት ጌታችን በገሠጻቸው ጊዜ እጅግ ግልጽ ሆኖ የተነገረ ጉዳይ ነው።

የተከበሩ ስዌህ በጻፉዋቸው ምዕራፎች ሁሉ ላይ ዛሬ የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለ መሆን መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ያብራሩልናል። በተጨማሪም ዘመናውያን ሰባኪዎች ብዙ ጊዜ በስብከታቸው ውስጥ የማያካትቷቸውን፣ በአገልግሎት ውስጥ የመሥዋዕትነትና የመከራ ስፍራ፣ በፈቃደኝነት ድህነትን መቀበል፣ የሕይወታችንን ቅድሚያዎች በትክክል የመለየት አስፈላጊነት፣ ሁኔታዎች ሲከብዱና የመሳሰሉ ችግሮች ሲከሰቱ ታማኝነትና ጽናት ያላቸው ስፍራ የተሰኙ መሪ ሐሳቦችን ጻጻሱ በመጽሐፋቸው ውስጥ ያካትታሉ። መጽሐፉ የድሮዎቹ መንፈሳዊ ጸሐፍት ‹‹ጥልቅ ሕይወት›› በማለት የሚናገሩትን ይዳስሳል። የምትመኙት በክርስቶስ ጥልቀት ውስጥ ያለውን እድገት ማግኘት ከሆነ፣ ከእነዚህ ገጾች የሚጠቅሟችሁን ብዙ ነገሮች ውሰዱ!

በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ይህን መጽሐፍ እንዲያነብ በሙሉ ልቤ ማሳሰብ እጅግ ደስ ይለኛል። ቶሎ ቶሎ ብላችሁ በጥድፊያ አታንብቡት። እያንዳንዱን መልእክት በሚገባ በውስጣችሁ በማብላላት በግልና በጥሞና ጊዜያችሁ አንዳንድ ምዕራፍ አንብቡ። ያኔ ሕይወታችሁን የሚያበለጽግ መንፈሳዊ ዕንቁ ሆኖ ታገኙታላችሁ። በትሕትና ራሳችንን ዝቅ አድርገን፣ ጌታችንን ይበልጥ ወደ መምሰል ደረጃ በእግዚአብሔር ጸጋ እንደግ!

የተከበሩ ዶክተር ማይክል ሸን

በመጽሐፍ ቅዱስ ትንታኔያዊ አስተምህሮ ፕሮፌሰር

እና

የቀድሞ የሲንጋፖር መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ርእሰ መምህር

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሕይወት ዘመን ተማሪ፣ አስተማሪና ሰባኪ የነበሩት የተከበሩ ስዌህ ዩ ክዎንግ ራሳቸው ተምሳሌት ስለ ሆኑበት መንፈሳዊ ባሕርይ የሰጡት የማያወላዳ አጽንኦት ስሜቴን በእጅጉ አነቃቅቶልኛል። ለሥነ መለኮት ተማሪዎች እርሳቸው ይሰጡ የነበሩት ምክር “እግዚአብሔር ይቀድማል፤ ትምህርት ይከተላል” የሚል ነበር። *የአገልጋይነት ሥርዓት* የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ለሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች፡- እግዚአብሔርን ማወቅ፣ እምነትን መለማመድ፣ ማንነትን መምረጥ ውስጣዊ የሆኑ መልካም ስሜቶችን ለመለማመድ ውጫዊ ችግሮችን መርታት የሚሉ ወሳኝ የሆኑ ትምህርቶችን ያቀርባል።

የተከበሩ ስዌህ በ1830 ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሕንድ ከሄደው የስኮትላንድ ሚስዮናዊ (የወንጌል መልእክተኛ) አሌግዛንደር ዳፍ (1806-78) ለወንጌል ሥራ ተመሳሳይ የሆነ ተቆርቋሪነትና ፍቅር ነበራቸው፡፡ ዳፍ ለመሞት ተቃርበው ሳለ ወደ አገራቸው በተመለሱ ጊዜ፣ በፕረስባይቴሪያ ሲኖድ ውስጥ የሚገኙትን ወጣት ትውልዶች መንፈሳዊ ዓርማ እንዲያነሡ ቀስቅሰዋቸዋል፡፡ ስዌህም “ጥሪና ተግባር” በሚል ርእስ ያሰሙት ድምፅ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

የምትከፍለውን ዋጋና የሚጠብቃትን ኣደጋ ከምንም ሳትቈጥር ሕዝቧን ለማዳን ስትል ሕይወቷን ለኣደጋ ኣሳልፋ እንደ ሰጠችው ኣስቴር ያሉ ወጣቶችን ዓለም ዛሬ ትፈልጋለች። ቤተ ክርስቲያንን የሚያነቃቁትን ብዙ ጅን ዌስሊዎችን እና ወደ ደቡብ እሲያና ወደ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን የሚያደርሱ ብዙ ዊልያም ኬሪዎችን እግዚአብሔር ያስነሣልን። የታላቁን ንጉሥ የጌታ ኢየሱስን መመለስ የምናስተናግደው ያን ጊዜ ብቻ ነው።

መ ቅ ድ ም

የተከበሩ ስዌህ ከሥራዎቻቸው ዐርፈዋል፣ ነገር ግን በእምነት፡- የጌታን ጥሪ ለመታዘዝ ትፈቅዳላችሁን? በሸክላ ሠሪው እጅ የተቀረጸ፣ በእሳት የተቃጠለና ለጌታ ጥቅም የተቀደሰ የክብር ዕቃ ሁኑ! በማለት አሁንም ባለማቋረጥ ጥሪያቸውን ያስተላልፋሉ፡፡

የአጎት ስዌህ የፍቅር ምክሮች

የተከበሩ ዳንኤል ራኦ
የካምፓስ ኢቫንጀልካል ፌሎሺፕ
ቦርድ ሊቀ መንበር



የተከበሩ ስዌህ ዩ ክዎንግ (እ.አ.አ.) ከ1971-1973 የታይዋን የካምፐስ ኢቫንጀልካል ፌሎሺፕ ሠራተኞች የሥልጠና መሪ እንዲሆኑ ተጋብዘው ነበር። በወቅቱ ባልደረቦቻችን በሙሉ "አጎታችን ስዌህ" በሚል ስያሜ ይጠሯቸው ነበር። የእርሳቸውን የትምህርት ክፍለ ጊዜ የተሳተፍሁ ስሆን፣ በሥልጠናው በእጅጉ ተጠቅሜበታለሁ።

ከዓመታት በፊት፣ በቻይናና ጃፓን መካከል በተደረገው ጦርነት ወቅት፣ መንፈስ ቅዱስ በቻይና በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ዘንድ ሥራውን አነሣሥቶ ነበር። በዚያን ጊዜ ተማሪ የነበሩት የተከበሩ ስዌህ በናንጂንግ ለሚገኘው የዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ኅብረት ሕይወታቸውን ሰጡ። ከዚያ በኋላ ጌታን ከስድሳ ዓመታት በላይ አገልግለውታል። ለእኔ ከመንፈሳዊ መካሪዎቼ አንዱ ነበሩ።

ለአጭር ጊዜ ብቻ አብሬአቸው ብቆይም፣ ከእርሳቸው የተማርኋቸው ትምህርቶች በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አብረውኝ ዘልቀዋል። የተከበሩ ስዌህ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ የሚያውቁና የእግዚአብሔርን ቃል የሚወዱ ሰው ነበሩ። የቅዱሳት መጻሕፍትን ክፍሎች የማብራራት ስልታቸው ቀላልና በተለይም አብርሆትን አፍላቂ ነበር። በዕለታዊ ሕይወትና አገልግሎት ረገድ እውነቱን ስለ መኖር ተግባራዊ ገጽታ ላይ ታላቅ አጽንኦት ይሰጡ ነበር። ጥልቅ መንፈሳዊ ግንዛቤ ስለ ነበራቸው ወደ አንድ ሰባኪ ሕይወትና የልብ ዝንባሌ በቀጥታ መድረስ ይችሉ ነበር። ዒላማቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ሙሉ በሙሉ የመተግባር ጉዳይ ነበር። ይህ በብዙዎች ዘንድ አድናቶትን ያስገኘላቸው ድርጊት ነበር። ትምህርታቸው ወደ ሌሎች ጠልቆ የሚገባ ስለ

ነበር፣ እርሳቸው የጌታን ፈለግ በሚከተሉበት ሰዓት ሰዎች በፈቃዳቸው እርሳቸውን ይከተሉ ነበር።

ሕይወታቸው ያልተወሳሰበና ሥርዓቱን የጠበቀ ነበር። በሥራ ላይም ሆነ በዕረፍት ጊዜያቸው ጥንቁቅ ሰው ነበሩ። ፊት ለፊት የሚናገሩና ደፋር ሰው ነበሩ። አዎን፣ ሲሉ አዎን፣ አይደለም ሲሉ አይደለም ይሉ ነበር፡፡ ይህን ፈጽሞ በቀጥታ የደርጉ ነበር። ይህ ሕይወታቸው ከወጣቱ ትውልድ መካከል ጌታን ለምናገለግል እንደ መልካም ተምሳሌት ጠቅሞናል። በካምፐስ ኢቫንጀሊካል ፌሎሺፕ በሚገኙት ሰዎች አስተሳሰብና ሕይወት ላይ ጽኑ ተጽዕኖ አሳርፈዋል። የተከበሩ ስዌህ በጌታ እቅፍ ውስጥ ያረፉት በ2004 ዓ.ም ነበር። ትምህርታቸውና ምሳሌነታቸው በትውስታዬ ውስጥ ገና ትኩስ ናቸው።

ይህ መጽሐፍ የብዙ ዓመታት የጽሑፎቻቸው ጭማቂ የሆኑ ሐሳቦችን ይዟል። የእግዚአብሔርን አገልጋዮች መንፈሳዊ ሕይወት የሚገነቡ ጥበቅ ምክሮቻቸውንና ትምህርታቸውን ያካተቱ 41 ምዕራፎች አሉት። ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለሕዝቡ ያላቸውን ጭንቀት በግልጽ የሚያሳዩትን እነዚህን ጽሑፎች ደግሜ ደጋግሜ አነብባቸዋለሁ። በእነዚህ አማካይነት በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አእምሮዬ የበራ፣ መንፈሴም ከፍ ያለ ሆኗል። በተለይ እግዚአብሔርን ለማገልገል ልቡ ያላቸው ሰዎች፣ ይህን መጽሐፍ እንዲያነብቡት እመክራቸዋለሁ። ይህን ውድ፣ በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ የሚጠቅማችሁን አበረታች ምክርና ማብራሪያዎች እንደምታነብቡ ተስፋ አደርጋለሁ።

ዶክተር ስታንሊ ሊንግ
የኤስ ላይ ኤም ምሥራቅ እስያ
አኅጉራዊ ዲሬክተር

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያለሁ ወጣት በነበርኩባቸው ወቅቶች በሚቹ የተከበሩ ስዌህ ዩ ክዎንግ የተካሄዱትን የተለያዩ ጀማ የወንጌል ስርጭቶችና መነቃቂያ ስብሰባዎች በመካፈሌ ክብር ይሰማኛል። የእርሳቸው ስብከቶችና ትምህርቶች በሕይወቴ ላይ ትልቅ አሻራ ጥለውብኛል። ወይዘሮ ሊሊ ስዌህ የባለቤታቸውን ስብከቶቻቸውንና መጣጥፎቻቸውን ለማሰባሰብ በወሰኑ ጊዜ ድጋፌን ለመስጠት እኔ የመጀመሪያ ሰው ነበርሁ።

ከአምስት ዓመታት የድካም ሥራ በኋላ፣ በተከበሩ ስዌህ የተጻፉ አምስት ርእሶች በቻይንኛ ታትመው በማየታችን ተደሰትን። ቀጣዩ ሥራችን ብዙ ሰዎች በሥራቸው ይባረኩ ዘንድ ከእነዚህ ጥቂቱን ወደ እንግሊዝኛ መተርጎም ነበር። "የአገልጋይነት ሥርዓት" የተሰኘው ይህ ልዩ መጽሐፍ የተጻፈው በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ ላሉ ሲሆን፣ ሌሎች ክርስቲያኖችም እንደሚጠቀሙበት እርግጠኛ ነኝ።

የተከበሩ ስዌህን ሥራ ከሌሎች የሚለየው የእርሳቸው መንፈሳዊነት ነው - እርሳቸው ሁልጊዜም ወደ ጌታ መቅረብ የሚፈልጉ ሰው ነበሩ። ከሌሊቱ ነዐ ሰዓት ተነሥተው መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናትና በመጸለይ ከጌታ ጋር ማሳለፍ ለእርሳቸው፣ ገና ወጣት እያሉ የለመዱት ዕለታዊ ሥርዓት ነበር። ባረጁና በታመሙ ጊዜ፣ ያንን ልምምዳቸውን ለመቀጠል ይፈልጉ ነበር፤ የሚያሳዝነው የጤናቸው መታወክ ያንን እንዳያደርጉ አልፎ አልፎ አግዷቸዋል።

የተከበሩ ስዌህ ያልተወሳሰበ ሕይወት ነበራቸው። ለዕለት ፍላጎታቸው እግዚአብሔርን በጥብቅ የሚታመኑና ለአገልግሎታቸው ያለ መታከት የሚጸልዩ ነበሩ። አገልግሎታቸው በኃይልና በተጽዕኖ አድራጊነት የተሞላው ለዚህ ነበር።

ኃጢአት ያደረገንና ያለ አግባብ የሚሄድን ሰው ለመገሠጽ ወደ ኋላ የማይሉ የእግዚአብሔር ባሪያ ነበሩ። ላይ ላዩን ኮስታራና ግትር ሲመስሉ፣ ነገር ግን ሁልጊዜ ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ቅድሚያ የሚሰጥ ትሑትና ደግ ልብ ነበራቸው።

እምነታቸውን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ የኖሩትን የተከበሩ ስዌህን የሚመስሉ ብዙ አገልጋዮች ምን ነው በኖሩ ብዬ እመኛለሁ።

የአርታዒው ማስታወሻ

በክርስቲና ካስቴሊ



የዚህ ሥራ አካል በመሆኔ በጣም ደስ ብሎኛል-መጣጥፎችን፣ የክፍል ትምህርት ጥራዞችንና በኢንተርኔት ላይ የሚሠሩ ሥራዎችን በመጻፍና በማረም ብዙ ልምድ አለኝ፣ ነገር ግን መጽሐፍን ከዚህ ቀደም መጽሐፍ ፈጽሞ አርሜ አላውቅም።

ይሁንና፣ በሥራው ሙሉ አርትኦት ለማካሄድ ያለኝ ንጹሕ ሥነ ጥበባዊ ፍላጎት ከልምዴ አናሳነት ያለፈ ሆነ። ምንም እንኳ ወደ አዲስ ቋንቋ ለመቀየር የሐሳቡን ፍሰት ለማስጠበቅ ብዙ ሥራ ያለበት ቢሆንም፣ የተከበሩ ስዌህ ጽሑፍ በግልጽ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ስለ ነበር፣ ከቃሎቹ በስተጀርባ ይህ ኃይል ይሰማኝ ነበር። ከሃያ ዓመታት በላይ ባለፍሁበት ቤተ ክርስቲያን እና በክርስቲያናዊ ትምህርት ውስጥ ከዚህ ቀደም ፈጽሞ አስቤው ወይም ሰምቼው በማላውቀው መንገድ፣ የተከበሩ ስዌህ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንና ምንባቦችን በአዲስ፣ እውነተኛ ትርጉም ይሞሏቸዋል።

በጊዜው እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዓላማ ማየት ባንችልም እንኳ፣ ቃሉንና ፈቃዱን ስለ መከተል ያላቸው ቀዳሚ የሆነ አጽንኦት ለእኔ እጅግ ጎልተው ከሚወጡት መልእክቶች አንዱ ነበር። ጠቃሚ ሰዎች ከመሆናችን በፊት በእትክልተኛው ተገርዘንና በሸክላ ሠሪው ተሚሽተን ለጌታ እንድንሠቃይ፣ የማያቋርጥና ኃይለኛ ተማጽኖ ለእኛ ያሰማሉ።

በወጣትነቴ በዚህ መጽሐፍ አንዳንድ ጊዜ እወቀስበታለሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በኃይል እሞላበታለሁ። እናንተም እንደ አንባቢያን ይህን መጽሐፍ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ጌታችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመቅረብ፣ ለማደግ የሚረዳችሁ ምንጭ አድርጋችሁ እንደምትጠቀሙበት ተስፋ አደርጋለሁ።

መግቢያ

ራስን የመስጠት የአገልግሎት ሕይወት

ባለቤቴ ወደ ዘላለም ቤቱ ከሄደ በኋላ፣ የእርሱን መጣጥፎች፣ ጽሑፎችና ያልታተሙ ማስታወሻዎችን አንድ ላይ ለማሰባሰብ ሙከራ አደረግሁ። ከሰባኪዎች አገልግሎት ጋር የተያያዙ ጽሑፎችን ለሥነ መለኮት ተማሪዎችና የወደፊት ሰባኪዎች “A Word to Preachers” (“ለሰባኪዎች አንድ ቃል”) የሚል መጽሐፍ አድርጌ አዘጋጀሁ። አገሪቱ የከሀደተ-እግዚአብሔርን እምነት በሚያራምድ መንግሥት ሥር ስለ ነበረች፣ በተለይም በቻይና አገር ያገለግሉ ለነበሩት ሰባኪዎችና መጋቢዎች ተምሳሌትነት እንደሚኖረው ልበ-ሙሉ ነበርሁ። ሰባኪዎች በዚህ ዘመን ለመዝለቅና እግዚአብሔርን ለማገልገል እምነታቸውን በጽኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ በማድረግ በክርስቲያናዊ ሕይወት የተለያዩ ዘርፎች መታነጽ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ እንደሚረዳቸው ተስፋ ነበረኝ። ከታተመ በኋላ፣ አንዳንድ አንባቢዎች በጣም ጥሩ መጽሐፍ መሆኑንና መንፈሳዊ ነገሮችን ለሚከታተሉ ሌሎች ወገኖችንም እንደሚጠቅም አስተያየታቸውን ለገሡ። *የታይዋን ካምፓስ ኢቫንጀሊካል ፌሎሺፕ* የተሰኘው ጎብረት የጎትመት መምሪያም፣ ሰባኪዎችን ብቻ ሳይሆን፣ መሪዎችንም ሊጠቅም እንደሚችል ተሰማው። እንግዲህ ከዚህ የተነሣ ርእሱን *የአገልጋይነት ሥርዓት* ወደሚል በመቀየርና ከማውጫው የአንዳንዶቹን ቅደም-ተከተል በመለወጥ የመጽሐፉን ተወዳጅነትና ተደራሲነት ለማስፋት ወሰኑ። በዚህ ሥራቸው በጣም ደስተኛ ስሆን፣ ጌታንም አመሰግነዋለሁ።

ከጎትመቱ ቀደም ብሎ የጽሑፉን ዝግጅት በምሠራበት ጊዜ፣ የዩ ክዎንግን ሕይወት አስታወስሁ። በመጀመሪያ ሆንግ ኮንግ በሚገኘው ጉዋንግዙ

መ ግ ቢ ያ

የመጽሐፍ ቅዱስ ሴሚኔሪ እርሱ ራሱ ለመማር ዕድል ያላገኘውን ትምህርት እንዲያስተምር ተጋብዞ ነበር። በመሆኑም ከእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ በፊት፣ ማድረግ የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነበር። በመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ይሄድና በፊቱ እየተንቀጠቀጠ ይንበረከክ ነበር። ከዚያም የእርሱን የእውነትና የጸጋ ቃል ማስተማር እንዲችል መንፈስ ቅዱስ ተገኝቶ በኃይል እንዲሞላው በጸሎት ይማጸን ነበር። በዚህ ዓይነት መንገድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ላይ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ትምህርቱን ያስተምር ነበር። ተማሪዎች ደግሞ የቃሉ ስርፀት ወደ እነርሱ መምጣቱ ይሰማቸው ነበር።

የእንግሊዝኛውን እትም በማዘጋጀቱ ረገድ፣ የታይዋኑ እትም ከታተመ በኋላ፣ በጥንቃቄ አነበብሁት። ቀላልና ተነባቢነት እንዲኖረው መስተካከል እንደሚገባው ተመለከትሁ። መጽሐፉ በእንግሊዝኛ የተማሩትንም ሊጠቅም እንደሚችል ስላሰብሁ በእንግሊዝኛ እንዲተረጎምም መነሣሣት መጣብኝ። የሚያርም አግባብ ያለው አርታኢ፣ ትርጕሙን ከዋናው አገናዝቦ በማንበብ የሚያርምና የእኔን እንግሊዝኛ የሚያሻሽል ሰው ጌታ እንደሚሰጠኝ ተማመንሁ። በዚህ ነገር ውስጥ የጌታ እጅ ስለ መኖሩ ምንም ጥርጥር የለውም። ይህ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ማስቻል የተገኘና የቡድን ሥራና ጥረት ፍሬ ነው። ስለ ሆነም፣ በመጀመሪያ የእጅ ጽሑፌን በታማኝነት በኮምፒዩተር ለተየቡ ሁለት ጓደኞቼ፡- ለሚሲስ ጎ ኬይ ሁዋ እና ቴይ ዋን ሲን፤ የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ምዕራፎች አርትኦት ለሠራው ለሚስተር ኢርቪንግ ኒኦ፤ በዚያን ጊዜ የቋንቋ ጥናቷን በሲንጋፖር ትሠራ ለነበረችውና የመጀመሪያውን አርትኦት ላደረገችው የዩ.ኤስ.ኤዋን ሚስ ክርስቲና ካስቴሊ ላስተዋወቁኝ ለዶክተር ስታንሊ ሊንግ የልብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በአርትኦቱ እንድትቀጥል በሁለቱም የእንግሊዝኛ እና የማንዳሪን ቋንቋዎች ከፍተኛ ችሎታ የነበራትን ሚስ ታን ኪም ሉዋንን ያስተዋወቀችኝን ሚሲስ ካአን አመሰግናለሁ። በትዕግሥትና ባለመታከት የመጀመሪያውን ጽሑፍ ትርጕም እንዲይዝ ለማድረግ የተቻላትን ሁሉ ሞክራለች። ፍቅር ስለ ተሞላው የመሥዋዕትነት ሥራዋ እንደዚሁም ከእርሷ ጋር ሆነው ስለ ረዱኝ ሁለት ጓደኞቿ፣ ሚስተር ጆኒ ኩን እና ሚስ ሼን ዩቸንን አመሰግናቸዋለሁ። በተጨማሪም የጽሑፉን የመጨረሻ ክለሳ ያደረጉትን ዶክተር

ፊል ማርሻልን እና ሚሲስ በሊንዳ ኤንጂን አመሰግናችዋለሁ። ጽሑፉን ለመጨረሻ ጊዜ በጥልቀት የመረመረችውን ሚስ ግሬስ ታንን ከልብ አመሰግናታለሁ። የኤስ ኢ ኤች ሲውን (SEHC) የተከበሩ ካአን እና ሚሲስ ካአን ስለ ተሳትፎአቸውና ምክራቸው፣ ሚስተር ቻአ ቲያንግ ሚንግንና በሲንጋፖር የሚገኝ የኤን ዋይ ፒን (NYP) ሚስስ ኢቫንጀሊን ቼንን፣ ለእኔ ስለ ነበራቸው ጭንቀትና ስላሳለፉት ጊዜ፣ እንደዚሁም ሚስተር ፒተርን ኢጋዥነት ስላለው ድርሻው አመሰግናቸዋለሁ።

ለማሌሺያው ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ (ዶክተር) ሁዋ ዩንግ፤ ለተከበሩ (ዶክተር) ማይክል ሼን፣ የሲንጋፖር መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የቀድሞ ኃላፊ፤ የተከበሩ ዳንኤል ራኦ፣ የታይዋን የካምፐስ ኢቫንጀሊካል ፌሎሽፕ የዲሬክተሮች ቦርድ ሊቀ መንበር፤ ለምሥራቅ እስያ ክፍለ-አኅጉራዊ የኤስ ኣይ ኤም ዲሬክተር ስታንሊ ሊንግ፤ ሁላቸውም ጥያቄዬን በቸርነትና በጸጋ ተቀብለው ለዚህ መጽሐፍ እያንዳንዱን በጣም ውድ፣ ከልብ የመነጨ የይነበብ ማስታወሻ ስለ ጻፉ በትሕትና ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመጨረሻም፣ አሁንም ይህ መጽሐፍ እንዲወለድ እጆቻቸውን አንሥተው ለጸለዩ ጓደኞችና የጸሎት ደጋፊዎች ሁሉ ቅን ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የሰማዩ አባታችን ከላይ የተጠቀሱትን እያንዳንዳቸውን በጸጋው ያስባቸው፣ ያስታጥቃቸው እንዲሁም ይባርካቸው። እርሱን ለማገልገል የጌታን ፋናዎች ለመከተል ፈቃደኞች እንዲሆኑና ከዚህም የተነሣ እርሱን ለመውደድ ይበረታቱ ዘንድ ብዙዎችን ለመባረክ ጌታ አምላካችን በዚህ መጽሐፍ ይጠቀም። ሁሉም ክብርና ዝና ለቅዱስ አምላካችን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ይሁን። አሜን።

የተከበሩ ሊሊ ሆ ስዊ ሆ (ሚሲስ ሊሊ ስዊህ)
በጡረታ ላይ ያሉ የኤስ ኣይ ኤም ሚስዮናዊት

የአእምሮ ሥርዓት



ክፍል አንድ

እነሆኝ

ከዚያም የጌታ ድምፅ፣ ‹‹እነሆኝ ማንን እልካለሁ ?
ማንስ ይሄድልናል›› ሲል ሰማሁት::
እኔም፣ ‹‹እነሆኝ፤ እኔን ላከኝ›› አልሁ::
(ኢሳይያስ 6፡8)

የኢሳይያስን የመጠራት ታሪክ በምናነብበት በማናቸውም ጊዜ፣ ልባችን ስለ እርሱ በአድናቆት መሞላቱ አይቀሬ ነው። በቤተ መንግሥት እንደ መወለዱ፣ ኢሳይያስ ምቹ ሕይወት መኖርና በፖለቲካው ውጤታማ የሆነ የሥራ መስክ መከተል በቻለ ነበር። እንዲህም ሆኖ ግን፣ እነዚህን ጥቅሞች ወደ ጎን ትቶ ተራ ሰባኪ ሆነ። ኢሳይያስ በማስተዋል መምረጡን ጊዜ አረጋግጦለታል። በእርሱ ዘመን የነበሩ ነገሥታት፣ የጦር አዛዦች፣ ነጋዴዎች ወይም ምሑራን ከተረሱ ዘመን የላቸውም። ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር የሠራው ሥራ ግን አሁንም ይኖራል።

ከ2,700 ዓመታት በፊት የተናገረው መልእክቱ፣ ዛሬም በሁሉም ስፍራ ላሉ ሰዎች መናገሩን ቀጥሏል። የእርሱ ምሳሌ ቍጥር ስፍር የሌላቸው ወጣቶች ለእግዚአብሔር ጥሪ “እነሆኝ፣ እኔን ላከኝ” ብለው በተመሳሳይ መንገድ ምላሽ እንዲሰጡ ያነሣሣቸዋል። ኢሳይያስ ከሌሎች የተለየ አእምሮ ስለ ነበረው ለእግዚአብሔር ጥሪ በፈቃደኝነት ምላሽ ለመስጠት ቻለ። የኢሳይያስን ልብ ስናስብ፣ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅራችን ይነቃቃል፣ ደግሞም እርሱን በማገልገልና በመከራ ጎዳና እንድንራመድ ልባችንም ይነሣሣል። የኢሳይያስን ልብ በተመለከተ መጠቀስ የሚገባቸው አንዳንድ ባሕርያት ያሉ ይመስለኛል።

ራስን ከማመጻደቅ ይልቅ ራስን መውቀስ

ኢሳይያስ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ የእግዚአብሔርን ክብር በራእይ ባየ ጊዜ፣ ስለ ራሱ ኃጢአተኝነት ራሱን ወቀሰ። ‹‹ጠፍቻለሁ፣ ወየልኝ!" በማለት ጮኸ። ፈጽሞ ንጹሕ አለመሆኑን በመረዳት፣ እግዚአብሔር በእርሱ ከመጠቀሙ በፊት የእግዚአብሔርን ማንጻት ለመቀበል ራሱን ባዶ አደረገ። ከዚህ ጋር ሲነጻጸር፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ አገልጋዮች ብዙ ጊዜ በዓይናቸው ውስጥ ያለውን ምሰሶ ሳይሆን፣ በሌላው ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ማየት የሚቀናቸው ተመጻዳቂዎች ናቸው። ስለዚህ የተሰበረ መንፈስ ያላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ዶክተር ጆን ሱንግ፣ በቻይና ባለው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ያስነሣቸው ታማኝ የእግዚአብሔር ባሪያ፣ የአድማጮቻቸውን ክፉ ሥራ በስብከታቸው አማካይነት ተናግረው ይገሥጹ ነበር። ሲታይ አድማጮቻቸውን ሁልጊዜ የሚቈጡ ይመሰሉ እንጂ፣ ነገር ግን የእርሳቸውን ስብከት የሰሙ ብዙዎች ንስሐ እየገቡ የዘላለምን ሕይወት ይቀበሉ ነበር።

በዚያን ጊዜ የዶክተር ሱንግን ስልት በመኮረጅ አንዳንድ ሰባኪዎች በከፍተኛ ድምፅ ኃጢአትን ይገሥጹ ነበር፣ ነገር ግን አድማጮቻቸው ንስሐ አልገቡም። የዚህ ልዩነት ምክንያት ዶክተር ሱንግ ሁልጊዜ በጸሎት በመቃተትና የገዛ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ የእግዚአብሔርን ቃል ከመስበካቸው አስቀድመው በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ዝቅ ስለማያደርጉ ነበር። በሌላ በኩል፣ እርሳቸውን ይኮርጁ የነበሩ ሰባኪዎች ሌሎችን ሁልጊዜ የመኮነንና የተመጻዳቂነት ዝንባሌ ስለ ነበራቸው ነው። ስለዚህ፤ ስብከታቸው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ያልተባረከ ስለ ነበር የንስሐ ፍሬ ማፍራት አልቻለም። የእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል መተላለፊያዎች እንድንሆን ካስፈለገ፣ የተመጻዳቂነትን ልምድ ከልባችን ውስጥ ማስወገድ አለብን።

ራሳችሁን ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ውደዱ

“ማንን እልካለሁ፣ ማንስ ይሄድልናል?” ብሎ የሚናገረውን የጌታ ቃል

ኢሳይያስ በሰማ ጊዜ ወዲያውኑ፣ “እነሆኝ፤ እኔን ላከኝ!” በማለት መለሰ። እግዚአብሔር ለሥራው የኢሳይያስን ስም ባይጠራም፣ እርሱ ግን እግዚአብሔር መልእክተኛ እንዳስፈለገው ስላወቀ፣ በደስታ ለእግዚአብሔር ዓላማ ራሱን አቀረበ። በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን የሚያምን ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው ለግላዊ ምኞቶች ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር ዓላማዎች ነው።

ዛሬ፣ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ብዙ ወጣቶች፣ እግዚአብሔር ገና እንዳልጠራቸው ብዙ ጊዜ ይናገራሉ፣ ስለ ሆነም ገና ጥሪውን ይጠባበቃሉ። መንፈሳዊ ትኩሳታቸው በጠፋበትና እንዲያውም የመጀመሪያው መሰጠታቸው እንኳ በተረሳበት ሁኔታ ከዓመት ዓመት መጠባበቃቸውን ይቀጥላሉ። የእግዚአብሔር ጥሪ ተሰምቷቸው ሲያበቃ ነገር ግን እንደ ጥሩ ሥራ፣ የቤተሰብ ተቃውሞና የንግግር ችሎታ እጦት የመሳሰሉ ተግባራዊ ጉዳዮች እግዚአብሔርን ከመታዘዝ እንዲያግዷቸው የፈቀዱ ሌሎችም አሉ። ልባችን በመንፈስ ቅዱስ እንዲበራ ከፈቀድን፣ ለዚህ ችግር መሠረታዊ ምክንያቱ ራሳችንን እጅግ መውደዳችንና ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር አናሳ መሆኑ ነው። ራስ ወዳድነት ብዙዎች እግዚአብሔርን ማገልገል እንዲፈሩ አድርጓቸዋል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ ላለመስማታቸው ምክንያቱ፣ በቤተ ክርስቲያን በቂ ሠራተኞች ስላሉ ሳይሆን፣ ነገር ግን ጥሪውን ለመስማት ወደ እርሱ አለመቅረባቸው መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

ዛሬ፣ መቄዶኒያዊ ጥሪ ከሁሉም የዓለም ክፍሎች እየተሰማ ነው። ብዙ ወጣቶች ለጌታ መከራ መቀበልን ስለሚፈሩ፣ ለእነዚህ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ችላ ይላሉ። ስለ ተኮነነው ሀብታሙ ሰው በጌታ ኢየሱስ እንደ ተነገረው ሰው ታሪክ ከገሃነምም እንኳ ጥሪ ይሰማል። ያ በሥቃይ ላይ የነበረው ሀብታሙ ሰው ዕረፍትን ለማግኘትና ላልዳነው ቤተሰቡ የሆነ ሰው ተልኮ እንዲሰብክ በመለመን ጮሆአል። ከእነዚህ ተማጽኖዎች ባሻገርም እንኳ፣ ጥሪውን አንሰማም። በተጨማሪም ጥሪውን የሰሙ፣ ነገር ግን ላለመሄድ ብዙ ምክንያቶችን የደረደሩም አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን፣ “እባክህ ሌሎችን ላክ፣ እኔን ግን ተወኝ” እያሉ ያሉ ናቸው። የዚህ ዓይነት የራስ ወዳድነትና የምስጋና-ቢስነት ምላሽ የቱን ያህል እግዚአብሔርን በጥልቁ እንደሚያሳዝን ልትገምቱ ትችላላችሁ!

በሰማያዊው ክብር ላይ አነጣጥሩ

ኢሳይያስ በንጉሣዊ ቤተሰብ ዘንድ እንደ መወለዱ መጠን፣ በቤተ መንግሥት ያለውን ሕይወት የተለማመደና በዚያ ያለውን ውበትና የልዑላን ቤተሰብ ሥልጣን ያወቀ ነበር። ይሁንና፣ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ የእግዚአብሔርን ክብር ባየበት ቀን፣ ልቡ ሙሉ በሙሉ ተማረከ። ሱራፌል ከእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቆመው በታማኝነት እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ አየ። ይህ ራእይ እግዚአብሔርን ማገልገል በምድር ላይ ካለ ሥራ ሁሉ የበለጠ መሆኑን እንዲገነዘብ አደረገው። ከዚህም የተነሣ፣ የዚህን ዓለም ክብርና ሀብት አቅልሎ አየ። በሰማያዊው ክብር ላይ ለማነጣጠርም ወሰነ። እግዚአብሔርን እስከ ሞቱ ድረስ በታማኝነት ያገለገለበት ምሥጢሩ ያለው እዚህ ላይ ነው።

ጌታ ኢየሱስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ፣ እርሱን ወደ ትልቅ ተራራ ወስዶ መንግሥታትን ክብራቸውን ባሳየው ዲያብሎስ ተፈትኖ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህ ምድራዊ ነገሮች ሁሉ በሰማይ ካለው ክብር ጋር ሊወዳደሩ እንደማይችሉ ስላወቀ፣ በጥቂቱ እንኳ አልተፈተነም። የዲያብሎስን ፈተና ተቃወመና የመስቀሉን መንገድና ራስን የመካድ መንገድን መረጠ። በዘመነ ታሪክ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በእጅጉ የተጠቀመባቸው በሙሉ፣ ሀብት፣ ዝና፣ የትምህርት ስኬቶች በልባቸው የመጀመሪያውን ስፍራ እንዲይዙ ላለመፍቀድ የወሰኑ የዚህን ዓለም ክብር የናቁ ሰዎች ነበሩ። ለጌታ ሲሠቃዩ፣ ልባቸውና አእምሮአቸው በላይ ወዳለው ክብር ያነጣጥራል። ጆን ዌስሊ፣ "የዚህ ዓለም ክብርና ሀብት በመንገድ ላይ የምንረግጠውን አቧራ ይመስላል" የሚል ዝነኛ አባባል ነበረው። ቀደም ሲል፣ ብዙ ሰባኪዎች በንጹሕ ልብ እግዚአብሔርን በመውደድ ብቻ ጌታን ማገልገል በመጀመራቸው እግዚአብሔር በኃይል ተጠቅሞባቸዋል። ይሁን እንጂ፣ እነዚሁ ሰዎች ቀስ በቀስ ለቁሳዊ ፍላጎት ተንበረከኩ፣ ዓለማዊም ሆኑ። የእግዚአብሔርንም ስም አጎደፉ። ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር እነርሱን መጠቀሙን አቆመ። የእነርሱ ውድቀት ለእኛ እንደ ማስጠንቀቂያ ያገለግለናል።

የእኔ ልባዊ ጸሎትና ተስፋ ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ የሰጡቱ በነቢዩ ኢሳይያስ ልብና ታማኝነት ተነቃቅተው ለዚህ ትውልድ ራእይና ሸክም ያላቸው አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው።